# የፋሺስት ኢጣሊያን ወረራ በመቃወም መስዋእት ለሆኑት ብጽእ አቡነ ጴጥሮስ ሀወልት ቆመላቸው

Radio Fana



አዲስ አበባ ግንቦት 1 2001 ( ሬዲዮ ፋና ) የፋሺስት ኢጣሊያን ወረራ በመቃወም መስዋእት አቡነ ጴጥሮስ የትውልድ ስፍራቸዉ በሆነችው ፍቼ ከተማ የመታሰቢያ ሀውልትና አወደ ምህረት ቆመላቸው፡፡ ሀውልቱን ዛሬ መርቀው የከፈቱት የኦሮሚያ ክልል ርእሰ መስተዳድር አቶ አባዱላ ገመዳና ብጽእ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ናቸው፡፡

በ1928 ዓም የፋሺስት ኢጣሊያን ወራሪ ጦር በመቃወም መስዋእት ለሆኑት ብጽእ አቡነ ጴጥሮስ የመታሰቢያ ሀውልትና አውደ ምህረት የቆመው ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ ነው፡፡

ለዚሁ ስራ የዋለው ገንዘብ በአገር ውስጥና በውጪ ባሉ ኢትዮጵያውያን ፣ ከጠቅላይ ቤተክህነትና ከእምነቱ ተከታዮች የተዋጣ መሆኑን የሰሜን ሸዋ ስላሴ አገረ ስብከት ሊቀጳጳስ በጽእ አቡነ ቀስጦስ ጠቁመዋል፡፡

መታሰቢያ ሀውልቱ የቆመው ላለውና ለመጭው ትውልድ አባት አርበኞች በደምና በአጥንታቸው የከፈሉትን መስዋእትነት ከማስታወስ ባሻገር ለነጻነትና ለአገር አንድነት መስዋእት የሆኑ ሁሉ አኩሪ ተግባር ፈጽመው ማለፋቸውን ትውልድ የማይዘነጋው መሆኑን ለማስገንዘብ ነው፡፡